# Einführung

## *መግቢያ*

### ● የዚህ መጽሃፍ አጠቃቀም

ይህ መጽሃፍ *Deutsch-warum nicht?* የተሰኘው ክፍል ሶስት የጀርመንኛ ቋንቋ ኮርሳችን አጃቢ ነው። እንደ ክፍል አንድና ሁለት ሁሉ የራዲዮ ስርጭቱን ለምትከታተሉ አጋዥ እንዲሆን እንጂ ብቻውን በራስ ማስተማሪያነት ተግባር ላይ እንዲውል የተወጠነ አይደለም።
ሁልጊዜ በመጽሃፉ ላይ ከማተኮራችሁ በፊት በቅድሚያ የራዲዮውን ስርጭት ለማድመጥ ሞክሩ። የአድምጦ ልምምዶቹ በያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ እጅግ ጠቃሚ በሆኑት ነጥቦች ላይ ታተኩሩ ዘንድ የሚረዱ ናቸው። ኮርሱን በምትከታተሉበት ጊዜ በግድ እያንዳንዱን ቃል ለመረዳት መጣር የለባችሁም። በአንጻሩ አንድ ድርጊት የት ቦታ እንደሚፈጸም፤ ማን ከማን እንደሚያወራ፤ ስለምን እንደሚነገርና ስለ ሰዎቹ ሁኔታ አድምጦ ለመረዳት መሞከሩ ይመረጣል። አትዘንጉ! ሁሉንም ቃላት ከጅምሩ መረዳት አይኖርባችሁም።

### ● በክፍል ሶስት ውስጥ ምን አዲስ ነገር አለ

ዋነኞቹ የቋንቋው ኮርስ ተዋናዮች በዚህ በክፍል ሶስት ውስጥም ይኖራሉ።

- **Andreas** ተማሪ ሲሆን በትርፍ ጊዜው ሆቴል አውሮፓ ውስጥ በእንግዳ ተቀባይነት ይሰራል።
- **Ex** እንዲት የፈጠራ ምስል ናት። የምትታይ ነገር አይደለችም። ሆኖም ድምጿ ጎልቶ ነው የሚሰማው። በቋንቋ ኮርሳችን ሁለተኛ ክፍል መጨረሻ ላይ ድንገት መሰወሯ ይታወሳል። አሁን ግን እንደገና ተመልሳለች። ሌሎቹ ተዋንያን መለያ ባህሪዋንና በየጊዜው ጣልቃ መግባቷን በሚገባ ለምደውታል።
- **Dr. Thürmann** የሚኖረው በርሊን ውስጥ ነው። ሆኖም የሆቴል አውሮፓ ቋሚ እንግዳ እንደሆነ ታውቃላችሁ።
- **Frau Berger** የሆቴሉ ሃላፊ ናት።
- **Hanna Clasen** የሆቴሉ ክፍል አጽጂ ናት።

የክፍል ሶስት ትምህርት አቀነባበር በመጀመሪያዎቹ ሁለት መጻህፍት ውስጥ ከታየው የተለየ አይደለም። በመጀመሪያ ወይይቶቹን ታደምጣላችሁ። ከዚያም የውይይቱ ይዘት ይብራራል። ቀጥሎም የሰዋሰው ማስረጃው ክፍል ይከተልና ውይይቱ እንደገና ይደገማል ማለት ነው።

እርግጥ በክፍል ሶስት ውስጥ የሚገኙት ውይይቶች ይዘት ከክፍል አንድና ሁለት ሲነጻጸር ይበልጥ ከበድ ያለ ነው።

የክፍል አንድና ሁለት ድርጊቶች የተፈጸሙት አኼን ውስጥ ሲሆን የክፍል ሶስት ሁለተኛ አጋማሽ ድርጊቶች ደግሞ የሚካሄዱት **Berlin** ውስጥ ነው። እነዚሁ ምዕራፎች የከተማይቱን ገጽታና ታሪክ የተመለከቱ መረጃዎችን ይጠቁማሉ። በርሊንን ይበልጥ እንድታውቁ የሚረዱ ታሪኮችንም ታደምጣላችሁ።

በክፍል ሶስት መጀመሪያ ላይ የኮርሱን ዋና ዋና ተዋንያን እንደገና እናስተዋውቃለን። የመጀመሪያዎቹን ሁለት የራዲዮ ኮርሶች ያላደመጣችሁ ሁሉ ትምህርቱን በሚገባ ለመከታተል ትችሉ ዘንድ ጠቃሚ የሆኑት የሰዋስው አቋማትም እንደገና ይደገማሉ።

- **የመጽሃፉ ይዘት**

**ሀ- የጀርመንና የበርሊን ታሪክ መረጃ**

ይህ ክፍል እ.አ.አ. ከ 1949 እስከ 1990 ዓ.ም. በምዕራባዊው ፌደራል ሬፑብሊክና በምስራቁ ዴሞክራቲክ ሬፑብሊክ ለሁለት ተከፍላ ስለኖረችው ጀርመን አጠር ያለ መሰረታዊ መረጃ ይሰጣል።

**ለ- ስለያንዳንዱ ምዕራፍ መረጃ**

**1- የስዋስው ማስረጃ**

በዚህ ክፍል በያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ የሚነሱት ዋነኛ ሰዋስው ነክ ነጥቦችና አባባሎች ምሳሌዎችን በማቅረብ ጠለቅ ባለ መልክ ይተነተናሉ። አባባል ወይም አነጋገሮቹ በየምዕራፉ ሰፍረው የሚገኙት ቀደም ባሉት ኮርሶች ክፍል አንድና ሁለት እንደተለመደው ሁሉ በጀርመንኛ ብቻ ነው። በተቻለ መጠን በየምዕራፉ ብቅ ባሉበት ቅርጽና በመዝገበ -ቃላት ውስጥ ተቀምጠው በሚገኙበት መልክ እንዲቀርቡ ተደርገዋል።

<u>ምሳሌ፡</u>

*Sie singt gern* የሚለው አረፍተ-ነገር የተቀመጠው በንዑስ አንቀጽ መልክ ነው። *Etwas gern tun:* ይህን በመጠቀም ሌሎች አባባሎችን ለመቅረጽ ትችላላችሁ። ለምሳሌ፡ *Er liest gern.*

**2- የያንዳንዱ ምዕራፍ ይዘት**

እነዚህ ይዘቶች በውይይት መልክ፣ በመረጃነት፣ በደብዳቤም ሆነ በዜማ መልክ ይቅረቡ ከሰዋስው ማስረጃውና የአነጋገር ዘይቤዎች ቀጥለው በጀርመንኛ ተቀምጠዋል። ሆኖም የመረዳቱን ተግባር ያቃልሉላችሁ ዘንድ አጠር ባለ መልክ በአማርኛ ይብራራሉ። ምናልባት አንዱ የራዲዮ ስርጭት ቢያመልጣችሁ ይዘቱን ከመጽሃፉ ልታነቡ ትችላላችሁ ማለት ነው።

**3- ቃላትና አባባሎች**

በያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ የተዘረዘሩት ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረቡ ቃላትና አባባሎች ብቻ ናቸው። ዝርዝሩ አዳዲስ ቃላትን ለምስሌ በበርቶልት ብሬሽት ጥቅስ ውስጥ የሚገኙትን የጠቀለለ አይደለም። በኮርሳችን ክፍል አንድና ሁለት ውስጥ ብቅ ብለው የነበሩት ቃላትና አባባሎች በድጋሚ አልቀረቡም።

**4- ልምምዶች**

አብዛኞቹ ልምምዶች በሰዋስው ነጥቦች ላይ የሚያተኩሩ ቢሆንም የቃላትና የአነጋገር ዘይቤን፣ መስቀልያ ጥያቄዎችንና የቃላት-አባባሎችን ትክክለኛ አጠቃቀም የሚመለከቱ መልመጃዎችም አብረው ተጠቃለው ይገኛሉ። የክፍል ሶስት መልመጃ በራዲዮው ኮርስ የተደመጡ ሃረጎችና አረፍተ-ነገሮችንም ይይዛል። አስፈላጊ ከሆነ በመጽሃፉ ውስጥ በያንዳንዱ ምዕራፍ የሰፈሩትን ውይይቶች ሙሉ ይዘት ልትመለከቱ ትችላላችሁ። አንዳንዱም በተወሰኑ

ምዕራፎች ላይ እንድታተኩሩ የምትጠየቁበት ጊዜ ይኖራል። የአብዛኞቹን ጥያቄዎች መልስ መጽሃፉ መጨረሻ ላይ ካለው የልምምድ መፍቻ ቁልፍ ውስጥ ታገኛላችሁ። አንድ ጥያቄ ብዙ መልሶች የሚኖሩት ከሆነ ደግሞ በመፍቻው ውስጥ ** ይህን ምልክት ተከትሎ የሚቀጥለው ማሳሰቢያ ይጠቀሳል። (ነጻ አቀራረጽን ለሚሹ ጥያቄዎች መፍቻው ውስጥ የተጠቃለለ መልስ የለም)

**ሐ- የሰዋሰው ማስረጃ**

ክፍል ሶስት ውስጥ የቀረቡት አዳዲስ የሰዋሰው ነጥቦች እዚህ ይተነተናሉ። የክፍል ሶስት ሰዋሰው ይዘት እንደሚከተለው ነው።

1. ቋሚና ቋሚ ያልሆኑ፣ እንዲሁም የረዳት ግሶች ሃላፊ ጊዜ መልክ
2. መስተጻምሮች

   ዋና አረፍተ-ነገሮችን ለማገናኘት ጥቅም ላይ የሚውሉ መስተጻምሮች፣ ለምሳሌ *und, aber, sondern.*

   ዋናና ታካይ አረፍተ-ነገሮችን ለማያያዝ ጥቅም ላይ የሚውሉት መስተጻምሮች *daß, weil*
3. የቅጽል እርባታ

**መ- የልምምዶች መፍቻ**

በዚህ ክፍል በያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙትን ልምምዶች በትክክል አጠናቃችሁ እንደሆን ለማነጻጸር ትችላላችሁ።

**ሠ- የውይይቶች ትርጉም**

ይህ ትርጉም ክፍል አንድና ሁለት ኮርሳችንን ላላደመጣችሁና በነዚሁ ውስጥ ያሉትን ቀጸም ሲል የተብራሩ ቃላትና የሰዋስው ይዘቶች ለማታውቁ ሁሉ ረዳት እንዲሆን ታስቦ የተቀናጀ ነው። የዜማዎችና የግጥሞች ይዘት በህጋዊ ምክንያቶች የተነሳ አልተተረጎመም።

**ረ- የቃላት ዝርዝር**

በዚህ ክፍል እንዲቀመጡ የተደረጉት በክፍል ሶስት ውስጥ አዲስ የሆኑት ቃላት ናቸው። በክፍል አንድና ሁለት ውስጥ የሚገኙት ቃላት በድጋሚ አልተዘረዘሩም። እያንዳንዱ ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰበት ምዕራፍ ቁጥርም በቅንፍ ውስጥ ተቀምጧል።

**ሰ- የግሶች ዝርዝር- ንውስ አንቀጽ፣ ሃላፊ ጊዜ፣ ፐርፌክት**

በዚህ ዝርዝር ውስጥ በክፍል አንድና ሁለት የተጠቀሱትን ጨምሮ መላው ግሶች ተጠቃለዋል። የግሶቹ በሶስት የተለያዩ ጊዜያት መልክ መቀመጥ ጠቃሚ የሆኑ አረፍተ-ነገሮችን ለመስራት ሰፊ ዕድል የሚሰጥ ነው።

| | |
|---|---|
| <u>ምሳሌ፡</u> | *kommen – kam – gekommen <sein>* |
| ንውስ አንቀጽ | *kommen* |
| ሃላፊ ጊዜ | *(er/sie) kam* |
| የቅርብ ሃላፊ | *gekommen* |
| | *sein* በቅንፍ ውስጥ መቀመጧ የሚያመለክተው *kommen* የምትለው ግስ በአሁን ጊዜ በተሟላው የቅርብ ሃላፊ መልክ ፐርፌክት እንደ መሆን ግስ ስራ ላይ መዋሏን ነው። |
| | *Er ist gekommen.* |

በመጨረሻ አንድ ማሳሰቢያ፡
ይህ ኮርስ በዓለም ዙሪያ በሚገኙ በርከት ባሉ አገሮች ቋንቋዎች የሚሰራጭ ነው። በመሆኑም በተናጠል በያንዳንዱ አገር፣ እንበል ለምሳሌ በኢትዮጵያ የቋንቋ፣ የማህበራዊ ኑሮና የባህል ገጽታዎች ላይ በተለይ ማተኮር ባለመቻላችን እናዝናለን። ችግራችንን እንደምትረዱልን ጽኑ ዕምነታችን ነው። በሌላ በኩል በጀርመንኛና በራሳችሁ ቋንቋ መካከል ያለውን ልዩነትም ሆነ መመሳሰል ለይታችሁ እንደምትደርሱበት አንጠራጠርም።

የቋንቋ ኮርሳችን *Deutsch – warum nicht?* አስደሳችና የተሳካ እንደሚሆንላችሁ ተስፋ እናደርጋለን!

Herrad Meese

# ጠቃሚ መረጃዎች

## 1 የጀርመን ታሪክ

የሚከተለው የጀርመን ታሪክ አጠር ያለ መረጃን ብቻ የጠቀለለ ይሆናል። የተወሰኑ የታሪክ ወቅቶችን አስመልክተው በዚህ በክፍል ሶስት ውስጥ የተጠቀሱ ይዘቶችን በቀላሉ
እንድትረዱ መሰረታዊ መረጃዎችን ለመስጠት የተወጠነ ነው። መረጃው በተለይ የጀርመንን ብሄራዊ ህልውናና አፈጣጠር ዋና መሰረቱ ያደርጋል።

919: የመጀመሪያው የጀርመን ግዛት ይቆረቆራል

ጀርመን ወደ 19ኛው ክፍለ-ዘመን የገባችው የተከፋፈለች ሆና ነበር

እናም በጊዜው ጀርመን በርከት ያሉ የልዑላን፣ መሳፍንትና ነገሥታት ግዛቶችን የያዘች ነበረች። የተለያዩት ሉዓላዊ ክፍላት ገዢዎች የራሳቸው ስልጣን ነበራቸው። አንድ ብሄራዊ ግዛት የማቋቋም ፍላጎት የተከሰተው እንግዲህ ከዚህ ወዲህ መሆኑ ነው።

1871 – 1918 ሁለተኛው የጀርመን ግዛት ወቅት

1870/71: የፍራንኮ-ፕራሺያ ጦርነት
1871: ሁለተኛው የጀርመን ግዛት በቨርሳይ ቤተ መንግሥት ውስጥ ይመሰረታል
1918: አንደኛው የዓለም ጦርነት ይፈጸማል፤ የጀርመን ግዛት ህልውናም ያከትማል

1919 - 1933 የቫይማር ሬፑብሊክ ዘመን

1919: የቫይማር ሕገ-መንግሥት
1919: የቨርሳይ የስላም ውል መፈረም

1933 – 1945 የብሄራዊው ሶሻሊዝም (የናዚው) አገዛዝ ዘመን

1933: አዶልፍ ሂትለር በቻንስለርነት ቃለ-መሃላ ይገባል
1939: ጀርመን ፖላንድን ወራ ትይዛለች፣ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ይከፈታል
1945: ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ያበቃል፤ ጀርመንም ትንበረከካለች
አሸናፊዎቹ አበር መንግሥታት ብሪታኒያ፤ ፈረንሳይ፤ አማሪካና ሶቪየት ህብረትም ጀርመንን በአራት ከፍለው ይይዛሉ

1949 –1990 ጀርመን ፌደራል ሬፑብሊክና ዴሞክራቲክ ሬፑብሊክ በመባል ለሁለት ተከፍላ ትቆያለች

1949: ፌደራላዊት ጀርመን ሬፑብሊክ ቦንን ርዕሰ-ከተማ በማድረግ ትቋቋማለች
ፌደራል ጀርመን የሰሜን አትላንቲኩን መከላከያ ድርጅት ናቶን ትቀላቀላለች

1949: የጀርመን ዴሞክራቲክ ሬፑብሊክ ምስረታ
ምስራቅ በርሊንን ርዕሰ-ከተማዋ ያደረገችው ምስራቅ ጀርመን የዋርሶው ቃል-ኪዳን ማህበር ዓባል ትሆናለች

ጀርመን በዚህ ጊዜ የተከፋፈለች ነበረች፤ በርሊንም እንዲሁ! የምዕራብ ጀርመን ነዋሪዎች ምስራቅ ጀርመንን መጎብኘት አይችሉም ነበር። የምስራቁ ወገን ነዋሪም ወደ ምዕራቡ ክፍል መጓዝ የሚፈቀድለት ነገር አልነበረም። አርግጥ ቆየት ብሎ ጡረታ የገቡ የምስራቅ ጀርመን ነዋሪዎች ወደ ምዕራቡ ወገን እንዲጓዙ ይፈቀዳል። ከ 1945 – 1957 ዓም 2.7 ሚሊ-ን የጀርመን ዴሞክራቲክ ሬፑብሊክ ነዋሪዎች፤ ከነዚሁ መካከልም አብዛኞቹ የሰለጠኑ ሙያተኞች ነበሩ፤ ሸሽተው ወደ ፌደራል ሬፑብሊኩ ክፍል ይገባሉ። ይህም ከጠቅላላው ህዝብ ቁጥር ሲነጻጸር 15 በመቶው መሆኑ ነበር። ከ 1961 ዓም ወዲያ በሁለቱ ሬፑብሊኮች መካከል የነበረው የወሰን ጥበቃ ይበልጥ ይጠናከራል። በሚሸሹ የምስራቅ ጀርመን ነዋሪዎች ላይ ተኩስ እንዲከፈት ሲታዘዝ የበርሊን ምስራቅና ምዕራብ ክፍላትም በግንብ ይለያያሉ።

| 3.10.1990 ምዕራብና ምስራቅ ጀርመን ይዋሃዳሉ |
|---|

ጀርመን ከዚያን ወዲህ የተዋሃደች አንድ አገር ናት። በርሊንም እንደቀድሞው መልሳ ርዕሰ-ከተማ ልትሆን በቅታለች።


## 2 የበርሊን ታሪክ

1470: በርሊን የብራንደንቡርግ ልዑል መቀመጫ ትሆናለች
1709: በርሊን የፕራሺያ ንጉስ መቀመጫ ትሆናለች
1871: በርሊን የጀርመን ግዛት ዋና ከተማ ትሆናለች
1939: ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ይጀመራል
1945: ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ያበቃል፤ በርሊንም በአራቱ አሸናፊ መንግሥታት በብሪታኒያ፣ ፈረንሳይ፣ አሜሪካና ሶቪየት ህብረት መተዳደር ትጀምራለች
1946: በመላው በርሊን ነጻ ምርጫ ይካሄዳል

| በርሊን ከ 1948–1989 ለሁለት ተከፍላ ትቆያለች |
|---|

1948: በርሊን በምስራቅና ምዕራብ ትከፈላለች
1948/49: የበርሊን እገዳ
ሶቪየቶች የበርሊንን መውጫ-መግቢያ መገናኛ መስመር ይዘጋሉ፤ አሸናፊዎቹ ምዕራባውያን መንግሥታትም አንድ ዓመት ሙሉ በአየር ምግብ ያቀርባሉ
1953: ምስራቅ በርሊን ውስጥ በሶሻሊስቱ መንግሥት ላይ የህዝብ ዓመጽ ይፈነዳል
1958: ምዕራብ በርሊን ነጻ ከተማ ትሆናለች
1961: በርሊንን ለሁለት የከፈለው ግንብ ይታነጻል
1963: የመጀመሪያው የይለፍ ውል
የምዕራብ በርሊን ነዋሪዎች በምስራቁ ክፍል የሚገኙ ዘመዶቻቸውን እንዲጠይቁ ይፈቀድላቸዋል
1968: የምዕራብ ጀርመን ነዋሪዎች ወደ ምዕራብ በርሊን ለመጓዝ ፓስፖርት፣ ወደ ምስራቅ በርሊን ለማቋረጥም የይለፍ ፈቃድ (ቪዛ) ያስፈልጋቸዋል
1989: ግንቡ ይገረሰሳል፤ የብራንደንቡርግ መተላለፊያም ይከፈታል
የምዕራብና ምስራቅ በርሊን ነዋሪዎች እንደገና ነጻ ሆነው ለመዘዋወር ይበቃሉ
1990: ግንቡ ጨርሶ ይነሳል

3 የበርሊን ካርታ


Berlin
Copyright © by
Kartographischer Verlag
Reinhard Ryborsch
D-63170 Obertshausen bei Frankfurt am Main
P. O. Box 2105 Tel. (06104) 7 90 39 Fax (06104) 7 53 56
Deutschland Germany

## 4 የዓመቱ ወራት

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Januar | ጥር | 7 | Juli | ሐምሌ |
| 2 | Februar | የካቲት | 8 | August | ነሐሴ |
| 3 | März | መጋቢት | 9 | September | መስከረም |
| 4 | April | ሚያዚያ | 10 | Oktober | ጥቅምት |
| 5 | Mai | ግንቦት | 11 | November | ሕዳር |
| 6 | Juni | ሰኔ | 12 | Dezember | ታሕሳስ |

Wann kommen Sie? Im Januar.

## 5 የኮምፓስ አቅጣጫዎች

Der Norden / ሰሜን
nördlich / በስተሰሜን

Der Westen / ምዕራብ
westlich / በስተምዕራብ




Der Osten / ምስራቅ
östlich / በስተምስራቅ

Der Süden / ደቡብ
südlich / በስተደቡብ

Wo liegt Aachen? Aachen liegt im Westen (von Deutschland).
Wo liegt Köln? Köln liegt nördlich von Bonn.
Köln liegt nordöstlich von Aachen.

Man ging durch das Brandenburger Tor von Osten nach Westen.
Berlin kann eine Brücke zum Osten werden.

## 6 አሃዞች ከመቶ እስከ ሺህ

100 = hundert
200 = zweihundert
300 = dreihundert
400 = vierhundert
500 = fünfhundert
600 = sechshundert
700 = siebenhundert
800 = achthundert
900 = neunhundert
1000 = tausend

101 = einhunderteins  202 = zweihundertzwei  311 = dreihundertelf
420 = vierhundertzwanzig  435 = vierhundertfünfunddreißig

100 = **Nominativ:** Das ist der hundertste Geburtstag,
das ist die hundertste Frage,
das ist das hundertste Buch.

**Akkusativ:** Er hat den hundertsten Geburtstag,
er stellt die hundertste Frage,
er kauft das hundertste Buch.

## 7 የዓመታት አሃዞች

የመጀመሪያዎች ሁለት አሃዞቹ ክፍለ-ዘመንን ያመለክታሉ። ለዚህም ነው ከመጀመሪያው አሃዝ ቀጥሎ መቶ = *hundert* የሚለው ቃል የሚታከለው።

| | | |
|---|---|---|
| 911 | = | neunhundertelf |
| 1871 | = | achtzehnhunderteinundsiebzig |
| 1961 | = | neunzehnhunderteinundsechzig |
| 1990 | = | neunzehnhundertneunzig |